# ወራሪው የሱዳን ጦር ድባቅ ተመቶ ተባረረ ፤ 8 የሱዳን ወራሪዎች ተማረኩ

**ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ**

**ግንቦት** 2 **ቀን** 2000 **ዓ.ም.** ( May 10, 2008 )

**ከጥቂት ቀናት በፊት የሱዳን ጦር የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ጥሶ በመግባት በጎንደር ክፍለ ሃገር በቋራ ወረዳ ያካሄደውን ወራራ ፣ ዝርፊያና ንብረት ማውደም ለመድገም ፤ በከባድ መሣሪያ የተደራጀው ይኸው ወራሪ የሱዳን ጦር ሐሙስ ሚያዝያ** 30 **ቀን** 2000 **ዓ.ም.** ( May 8, 2008 ) **በዛው በጎንደር ክፍለ ሃገር ፣ ታች አርማጭሆ ወረዳ ዘልቆ በመግባት ከአብደራፊ ከተማ ወጣ ብሎ በስተምዕራብ በኩል ከገላአሉባን እና ጓንግ ወንዝ መካከል የሚገኘውን የአቶ አራዶም ተወልደ መድህን የእርሻ ልማት በመዝረፍና በማቃጠል ላይ እንዳለ ፤ የሃገሩን ዳር ድንበር በቆራጥነት ለማስከበር በከፍተኛ ወኔ ታጥቆ የተነሳው የአካባቢው ሕዝብ የክተት ጥሪ በማሰማት ከወራሪው የሱዳን ጦር ጋር ከፍተኛ ፍልሚያ አካሂዶ ድል ከተቀዳጀ በኋላ ፤ ወራሪውን ጦር እየተከታተለ ድባቅ በመምታት ወደ መጣበት አባሮ ከመመለሱም በላይ ፤ በውጊያ ላይ የነበሩ** 8 **የሱዳን ወራሪዎችን ማርኮ በቁጥጥር ሥር አውሏል።**

**እንደሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ለሃገሩ ነፃነት ቀናዒነት ያለውና የሃገሩን ዳር ድንበር በማስጠበቅ ከፍተኛ ተጋድሎ የሚያደርገው ይኸው የአካባቢው ሕዝብ ዳር ድንበሩን ከወራሪው የሱዳን ጦር ለማስከበር በሚያካሂደው መራራ ትግል የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ጣልቃ እንዳይገባበት ለአካባቢው ባለሥልጣናት አስታውቋል።**

**የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!**

**የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር የአባቶቻችን ቃል-ኪዳንና አደራ አለብን!**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

**የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ**
**ኢሜል አድራሻ/ E-mail: leethiopia@yahoo.com**